ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በህዳር 19 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የወደቀን አንሳ ፤ የሞትን አትርሳ

ሰማዕቱን የማይራሳ፤ የወደቁትን የሚያነሳ ትውልድ የምታፈራ ሀገር ምንኛ የተደለች ነች ? ኢትዮጵያ ሀገራችንስ ይህ ዕድል አለኝ ብላ ትፅናናለች እንዴ ? ወይስ ዕድሉ እንዲኖራት ትመኛለች? ሰማዕታቱ ተረስተው ፤ ዐርበኞቿ ተዋርደው፤ ታስረው፤ በዐደባባይዋ ተሰቅለው፤ ቤተዘመዶቻቸው ተብትነው መቅረታቸውን ነው? ወይስ አይ፤ ይህ ሁሉ አልተፈፀመም ብላ በዕርግጠኘነት ልትናገር ትችላለች? እንደ ድመት፤ የራሷን ልጆች ትበላለች ? ወይስ፤ ልጆቿን ከአጥፊዎች ታድናለች? የሞተላት ፆም አድሮ፤ የገደላት - የከዳት ተንቀባርሮ ፤ የአመናት- ያፈቀራት አንገቱን ቀብሮ፤ ሌባ -ቀጣፊው ሀብቷን ዘርፎ ፤የሚኮበልልባት ሀገር ነች ? ወይስ አይደለችም ? ለእነኝህና ለተመሳሳይ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ልትሰጥ የምትችል ራሷ ሀገራችን ነች።

" የሰው ሞኝ አንድ እንጭት ያስራል " እንደሚባለው ተረት፤ ሀገሪቱ ግዑዝ ስለሆነች፤ እርሷ ልትጠየቅ አይገባትም ሊባል ይቻል ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የልጆቿን ደህንነት ባለመጠበቋ ግን፤ በኃላፊነት ከመጠየቅ አታመልጥም የሚሉ ዜጎቿ ቁጥር ቀላል አይደለም። እንዲያውም ከዚህ አልፈው -ተርፈው፤ ሀገራችን በድላናለች ብለው በፍረድ ቤት ለመክሰስ የሚያስቡ እንዳሉ ተደጋግሞ ይሰማል፡፡ በዚህ ፋይል ተከፍቶባት ብትከሰስ፤ ጠበቃ የሚቆምላት ማን ይሆናል ? ጉዳዩ የኀሊና ጥያቄም ጭምር በመሆኑ፤ ሁሉም ዜጎቿ ሊያስቡበት ይገባል !

ትላንት የወደቀውን የሚያነሳ ፤ ሠማዕታቱንም የማይረሳ ትውልድ፤ የነገን ጀግና ለማፍራት አይቸገርም። የትላንት ጀግኖችን ያከበረ ፤ መጭ ጀግኖችን ለማብቀል ተስፋው ሰፊ ነው። ጀግና እየተተካ መሄድ፤ ለሀገር ነፃነት ዋስትና ይሆናል። ይኸ ከሆነ ምድሪቱም የአናብስት ሀገር የሚል ስምን ታተርፋለች ። በጠላት አትደፈርም። ለማንም የሥልጣን ጥመኛ አትገዛም ። ያ ከሆነ ደግሞ ፤ የሕዝብ ዴሞክራስያዊ ጥያቄ በዘለቄታ መልኩ ሊመለስ የሚችልበት ዕድል ሰፊ ይሆናል ።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመመስረት የሚቻለው ግን፤ ሁሉም ዜጎች በአንድነት መንፈስ ሀገራዊ ዕሴትን ፤ አንግበው ቆርጠው ሲነሱ ብቻ ይሆናል። ይህ ቁርጠኝነት ካለ፤ የታሰበውን ዐላማ ለመምታት የሚያገጥመውን ተግዳሮት ሁሉ፤ በቀላሉ ተቋቁሞ በኀብረት ማስወገድ ይቻላል ። የሀገርን ችግር በዘላቂ መልኩ ማስወገድ የሚቻለው ደግሞ፤ ራዕይ ያላቸው ሕዝቡ ያፈራቸው ሀገር ወዳድ ሰዎች ወደ ፖለቲካው ምኅዳር ሲመጡ ይሆናል። የሀገሪቱ ፖለቲካ ምኅዳር ትርጉም የሚኖረው፤ ሀገራዊ ዕሴትን ፤ከዘውግ አመለካከት ጋር ሚዛናዊ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ማስተናገድ ሲቻል ነው ። ሁለቱን አቻችሎና አስታርቆ መጓዝ አስፋላጊ ብቻ ሳይሆን፤ አስተማማኝና ዘላቂ መፍተሄን ለማረጋጥገም ጭምር ነው።

ሀገራዊና ዘውጋዊ ፖለቲካን በሚዛን አስገብቶ ማስተናገድና አቻችሎ የመሄዱ ዕሳቤ፤ ለነገ የሚተላለፍ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም፤ ኢትዮጵያ፤ ጉራማሌ ዜጎች የሚኖሩባት ሀገር በመሆኗ ነው። ጉራማሌነት ደግሞ የአብሮነት ኅልውና መገለጫ በመሆኑ፤ አብሮነትና ኅልውና ተነጣጥለው ሊታዩና ሊስተናገዱ አይገባም የሚለው አባባል የብዙሃን ዜጎች ዕምነት በመሆኑ ነው። ብዙሃንነት፤ ለአብሮነት ጥንካሬን እንጅ ድክመትን፤ ውህደትን እንጅ መለያየትን ያስከትላል ተብሎ በብዙዎች ዘንድ አይታመን ።

ለዚኽ አባባል እንደ ህያው ማስረጃ የሚጠቀሰው የህንድ ሥርዓተ -መንግሥት ፤ ፌዴራላዊ አወቃቀርና አስተዳደር እንደሆነ በብዙ የፖለቲካ ልሂቃን ይታመናል። የተለያዩ ኀሳዎችን ፤ ዕምነቶችን ፤ ቋንቋዎችን ፤ ባኅሎችና ታሪኮችን የተላበሱት የኅንድ ዜጎች፤ ባንድ ታላቅ መለከዐ -ምድር ላይ በስምምነት መኖራችው ነው ። ባንድ ሀገር አብረው እንዲኖሩ ያስቻላችው ዐብነት፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት ስለአላቸው ነው። ይኽም፤ በሩቅ ምሥራቅ ታላቁ ዴሞክራሲ

የሚባለውን ስም ጎንድ እንድታገኝ አድርጓታል። ጎንዶች፤ ሀገራዊና ዘውጋዊ ዕውነታን በሚዛን አስቀምጠው ተቻችሎ በመኖራቸው ሌሎች ተመሳሳይ ይዞታና ብኅርይ ባላቸው ሀገሮች ዘንድ ፤ እንደ መልካም ምሣሌ ተቆጥረዋል። ጎንድ፤ በመሬት ስፋትም ሆነ በህዝብ ብዛት ከኢትዮጵያ ትበልጣለች። ካምስት መቶ ዐመታት የእንግሊዝ ቅኝ ተገዥነት በኋላ፤ ሕንድን ነፃ ያወጧት መሪዎቿ፤ የተከሉት መሠረት፤ ሀገራዊና ዘውጋዊ ዕውነታን በማጣመር ሚዛናዊ የሆነ ውኅደት ስር እንዲሰድ ጠቅሟቸዋል።

የአንድ ሀገር የመጀመሪያውና የመጨረሻው ሀብት ሕዝቡ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። የሀገራችን ሕዝብ ቁጥር ከመቶ ሚሊዮን በላይ እንደሚሆን ይገመታል። የሀገራችን ቆዳ ስፋትም ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። የተፈጥሮ ሀብቷም ገና ያልተነካና መጠነ ሰፊ ነው ይባላል። ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ፤ የባለ ሰፊ ሀብትና ታላቅ ሀገርን አካትቶ መገኘት ቢያስ ቢያስ ሦስት ጥቅሞች ይኖረዋል።

**1ኛ.** ከውጭ ጥቃትና ጸጥታ ሁከት አኳያ፤ እንዲሁ በቀላሉ ሊደፍረው አይችልም። ሀገራዊ ህልውናውንም ሆነ ሉዓላዊነቱን ሊፈታተነውና ሊዳፈረው የሚችል ኃይል እምብዛም ይሆናል። ይልቁንም ለአካባቢው ደኅንነትና መረጋጋት የራሱ ድርሻና አስተዋፃኦ ይኖረዋል። በሌሎቹ ሳይደፈር፤ እርሱም ሌሎቹን ሳይደፍር ፤ ግን ደግሞ፤ ተፍርቶና ተከብሮ በሠላም የመኖር ቁመና ይኖረዋል።

**2ኛ.** በምጣኔ ኃብት ደረጃ ቢሆን፤ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት፤ ማዕደናት የርሻ ሰብል፤ የኢዱስትሪ አቅርቦት የማፍራት ዐቅሙ የጠነከረ ነው። ከውጭ ለሚገባ ተፈላጊ ዕቃ ለማስተናገድ የሚችል ሰፊ ገበያ ስለሆነ ፤ አካባቢና ቀጠናዊ ማዕከል ይሆናል። ከውጭና ለውጭ ንግዶች መገባባያ ማዕከልነቱ ትልቅ ነው። የባኅል፤ የትምህርት፤ የማኅበራዊና የመረጃ ልውውጥ የሚከናወንባቸው ተግባራት በቀላሉ አይገመቱም። የኢኮኖሚ ኃይል ሞተር ሆኖ አንቀሳቃሽ ጉልበቱ ጣንካሬው ብርቱ ይህናል ።

**3ኛ.** ሰፊ የሕዝብ ቁጥርና ግዙፍ የመሬት ስፋት ያለው ሀገር፤ በዐለም አቀፍና በአካባቢ ደረጃ፤ የሚጫወተው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ሚና ፤ ተፅዕኖ ፈጣሪ ኃይል ሊያደርገው ይችላል። በሚጫወተውም ሚና ፤ መስኅብ መሆን ከቻለ፤ ተፈላጊነቱ አስደማሚ ይሆናል። በተለይም ደግሞ፤ የተፈጥሮ አቀማመጡ ስትራተጂያዊ ከሆነ፤ በጠቃሚነቱ የዐለም አቀፍ ማዕከል የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው። ሠላም ለማስከበር የበኩሉን አውንታዊ ሚና ሊጫወት ይችላል። በተቃራኒው ደግሞ፤ በራሱ ላይ የሠላም ማጣት ትንኮሳ ከተደረገበት፤ " ሠላምን ላለማጣት ለጦርነት ተዘጋጅ " የሚለውን አስተምህሮ አይዘነጋም።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ፤ ሦስቱን መስፈርቶች የምታሟላ መሆኗን አንጠራጠርም። በመሆኗም፤ የዜጎቿን መብትና ነፃነት አክብራ፤አንድነቷንና ሉዓላዊነቷንም ጠብቃ በብልፅግና ጎዳና ከመጓዝ በስተቀረ ሌላ አማራጭም ሆነ አቋራጭ የላትም ። ዜጎቿም ይኽንን መሠረታዊ ሀቅ ዕምነው መቀበል አለባቸው። ታላቋን ሀገራቸውን በታናናሽ ክልሎች ሸንሽነው እንደ ቅርጫ ሥጋ ከሚቦጫጭቋት ይልቅ ፤ በምልዕነቷ አንከባክበው በማያዝ፤ የምታበርክትላቸውን የጋራ ሀብት በጋራ ከመጠቀም የተሻለ ሌላ ምርጭ ሊኖራቸው የማይችሉ መሆናቸውን ተረድተው ፤ ለዘላቂ መፍተሄ መረባረብ አለባቸው ።

የሃያ አንደኛው ከፍለ ዘመን ክስተት የሚያመልክተው ይህንኑ ነው። ይህች ሀገር፤ ልኅልውናዋን ለማስከበር፤ ልማቷንም ለማስቀጠል፤ የዜጎቿን ኑሮ ለማሻሻል፤የወደፊት ብሩኅ ተስፋዋን ዕውን ለማድረግና በዐለም ዐቀፍ ደርጃ የሚገባትን ቦታ ለማያዝ የምትችለው በታላቅነቷ ተከብራና ተፍርታ መኖር ስትችል ነው። ለዚኽ ዐብነቱ ደግሞ በደሞክራሲ ሥርዓት የተገነባ ሕዝባዊ መንግሥት ስትመሰርት ብቻ ይሆናል። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት ባንድ ቀን ዠምበር ዕውን ሊሆን አይችልም። መሠረቱ ከተጣለ ግን ፤ ያንን ሥርዓተ መንግሥት ማግኘት ዕሙን ነው።

ወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመጣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በመፋፋም ላይ መገኘቱን ያመለክታል። እንቅስቃሴው አውንታዊ ድጋፍ ያልተለየው ቢሆንም፤ የሕዝብ ሙሉ ተሳትትፎ እንዲያገኝ መረጋገጫ የሚታይበት ይደለም። ዳር ሆኖ በመደገፍና በንቁ ተሳታፊነት መካከል ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይኽንን

ተገንዝቦ ለህዝባዊ ተሳትፎ ተገቢውን አጽንኦት መስጠት አግባብነት አለው። ያለ ሕዝቡ ሙሉ ተሳትፎ፤ የታሰበው ሥርዓተ ደሞክራሲ ሊሰፍን ከቶ አይችልም። ይህን ለማለት በቂ ማስረጃዎች አሉ ።

ሁለት ተመሳሳይ መልካም ዕድሎች፤ ሕዝቡን አምልጠው ቀርተዋል።እነርሱም፡ አንደኛው የካቲት 1966 ዓም ዐብዮት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የግንቦት 1981 ዓም ናቸው። ሁለቱም በሕዝባዊ ዐመፅ የተገኙ መሆናቸው ባይካድም፤ሕዝቡ በቂ ዝግጅትና ድርጅት ሳይኖረው ቀርቶ፤ ዕድሉን በፀረ ሕዝብ ኃይሎች ተነጠቀ። " ከሞኝ በራፍ ፤ብልጦች ሞፈራቸውን ቆረጡበት! " መፈሩን መቁረጣቸው ብቻ ሳይሆን፤ ሕዝቡንም ጭምር ቆርጠው፤ ሀገሩንም ቆራረጡበት። የታገለለትን ዴሞክራሲያ አንድነቱን ሳይሆን፤ የሚጠላውንና የሚቃወመውን የቋንቋና የዘር ልዩነት አመጡበት። ጥላቻንና ፍጅትን፤ ክፍፍልንና መለያየትን አሰፈኑበት። ሕዝቡ ግን አምፆ በመነሳት ፤ የሚፈልገውንና የሚጠቅመውን መረጠ። ላንነደቱ ቆርጦ ተነሳ። በዐመጽ የተደገፈ ሠላማዊ ሽግግር ማድረግ እንደሚቻል በተግባር አረጋገጠ።

ሕዝባችን፤ የተገኘውን ሠላማዊ ሽግግር ለውጥ ሳይደናቀፍ ግቡን እንዲመታ ይፈልጋል። ለዚኽም፤ የለውጡ ደጋፊ ብቻ ሳይሆን፤ በሂደቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን አጥብቆ ይፈልጋል። ለውጡን አንዳይነጠቅና ተስነካክሎ እንዳይቀር ለመከልከል የሚያስችለውን ቁመና ማግኘት ይፈልጋል ። ምክንያቱም መብቱ ስለሆነ ነው። መብትን ማስከበር ደግሞ ተፈጥሯዊ ነው። መብት አስከባሪ ጀግና የሌላት ሀገር እንዳትባል ፤ ኅብረተሰቡ፤ በያለበት የራሱን የነጻነት ዐርበኛ ማውጣት እንጅ፤ ያለፉትን መሥዋዕታዊ ጀግኖቹን እየረሳ፤ አዲስ ዕርበኛ ሊያበቅል አይችልም።

" ጨለማን ከመርገም፤ ሻማ እያበሩ ጽለመትን መግፈፍ " በአያሌው ይጠቅማል። ላለፈው ተስካር ምሾ መደርደር፤ ለመፃኢው ሠርግ ድግስ አብርክቶ አያመጣም። ይህ ሰለተባለ ግን የለፉትን ሠማዕታት መርሳት ማለት አይደለም ። የሠማዕታቱን ግደልና መሥዋዕት፤ ለፖለቲካ ሥልጣን መቆናጠጫም ሆነ፤ ለተለያዩ ዐላማዎች መምቻ ለመጠቀም መሞከር፤ ሀገራዊም ታሪካዊም ወንጀል ነው።ይኽንን ክስተት ዛሬ የመደምርን ጥሪ ምላሽ በመስጠት ላይ በሚቅለበለቡ ቡድኖች ሲንፀባርቅ እየታዘብን እንገኛለን። ለአላፊ -ጠፊ ብቻ ሳይሆን፤ ከታሪክ ዝቅተኛ ወለል በታች የሚከትትና በተትኪው ትውልድ ዘንድ እንደ አሳፋሪ ምሣሌ ተቆጥሮ ሲጠቀስ የሚኖር ነው። " ያወደቀን አንሣ፤ የሞተን አትርሳ " ሲባል፤ የራስንም አኩሪ ታሪክና አሰደማሚ ገድል ጭምር፤ አክብረህ እያስከበርክ ቆይ ማለትም ጭምር ነው።

ገናና ታሪኩን ፤ በደም በመሠዋዕትነት የፃፈው ያ ትውልድ፤ በጊዜያዊ የፖለቲካና የምጣኔ ጥቅማ ጥቅም ሊበረዝ አይችልም። የሀገሩንና የሕዝቡን ሁለንተናዊ ጥቅም ከማስቀደም የተለየ በቀፍላጎት አልነበረውም ። ለሀገሩና ለሕዝቡ የነበረውን ፍቅር በመሥዋዕት አስመስክሯል።ኢትዮጵያ ሀገሩና ሕዝቧ ጉራማሌ መሆናቸውን አምኖ ቢቀበልም፤ ጉራማሌነታቸው ሀብታቸውና ጥንካሪያቸው እንጅ ፤ለመከፋፈልቸውና ለመለያየታችው ምክንያት አይሆንም ሲል፤ አምርሮ ታግሏል። ይኽም ውድ ዋጋ አስከፍሎታል። ኢትዮጵያዊነት ዐልፋ-ዖሜጋ [ው] ነበር፡፤ አሁንም ይኽንን ዕምነት ናንግቦ ቀጥሏል። በዕምነታቸው እንስከ መጨረሻ ፀንተው የሚቆዩ ፤ብፁዐን ናቸውና፤ ያንን የድል አክሊል፤ ለአላፊ ጠፊ ጉዳይ አይለውጡትም ። " በሬ የሚስበው በአንገቱ ሳይሆን፤ በሆዱ " እናም ደግሞ ፤ " የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ። " የሚለው ይትብሃል ባንስተውም፤ አኩሪ ታሪክን በሆድ መለወጥ ግን የማይሞከር ባኅሪያችን ነው።

ምክንያታዊ ነጥቦችን እያነሱ መቃወም፤የበሳል ፖለቲካ ነፀብራቅ እንጅ፤ የአክራሪነትና የፅንፈኝነት ባኅርይ ተድርጎ ሊተረጎም አይገባውም። ይኽ ካልሆነ፤ ማንም ቡድን ጨቋኝ ሥርዓትን እንዳይቃውም የሚያደርግ አሸማቃቂ ፕሮፓጋንዳ ከመሆን አያልፍም። የቅስም ሰባሪ ፕሮፓጋንዳ ሰልባ ለማድረግ የሚደርገው ጥረት የሚጠቅመው ፤ ለወገቡ- ሽመድማዳዎች እንጅ፤ ማንነታችውን በመራራ ትግል ላሰመሰከሩና የተመከሮ ፀጋን ለተላበሱ ኢትዮጵያውያን ኃይል አይሰራም ። ድምፃቸው ለታፈነባቸው ድምፅ፤ ጥቃት ለሚደርስባቸው፤ አልኝታ፤ ለሟቾቹ ቤተሰቦች፤ ፤ አስተዛዛኝና አበርታች፤ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ፤ ፈጥኖ ደራሽ መሆናችንን በግብር እያገለጽን፤ ያለውን አገዛዝ በጀርባ ሆኖ የሚያሽከረክረውን የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ተመንግሎ አስኪፈልስ ድረስ ትግሉን መቀጠል ይመረጣል። አምባገነን አጋዛዝን አሽቀንጥሮ ለመጣል ደግሞ፤ ሌላ አማራጭና አቋራጭ አይኖርም። የሕዝብን መብቶች እየረገጡ የሚገዙ አምባገነኖች ፤ የሚመኙትን ሠላም ሊያገኙ አይችሉም። አይገባቸውም። የኀሊና ዕረፍት ሳያገኙ፤ እንዲሁ በስጋትና በጭንቀት ወስጥ ሆነው እንደባነኑ ይጠፏታል። እስከሚጠፉ ድረስ ግን፤ የፖለቲካ ሥልጣን፤ የኢኮኖሚ ሀብትና በጠቅላላውም የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ሕይወት

በሙሉ ተቆጣጥረው ይቆያሉ። በመጨራሽ ግን፤ በሕዝብ ዐመፅ ሁሉንም ተነጥቀው ታሪክ ወደ ጣለባቸው አዘቅት ይወርዳሉ።

አምባገነኖችን ወደ ከርሰ መቃብራቸው ለማስገበት ግን ከባድ መሥዋዕትን የሚጠይቅ ትግል ማካሄድን ይጠይቃል። የኸንን ተግባር በግንባር -ቀደም ለመፈፀም ወጣቱ ትውልድ እንደሆነ ትላንትም በታሪክ ተስክሯል። ዛሬም ይኸው በመደገም ላይ ይታያል። የወያኔን ዘረኛ ሥር ዓት ከስር-መሰረቱ እንዲናጋ ያደረገው፤ የፋኖ ዕርበኛና የ ቆሮ ተጋዳይ ወጣት ትውልድ ነው። ታሪክ የጣለበትን የትውልድ ኃላፊነት በሚገባ እየተወጣው ይገኛል። የትውልድ ቅብብሎሹን በኅብረት ተቀብሎ እያስተነገደው በመሄድ ላይ ነው። ሀገራችን የወላድ መካን አልሆነችም። ወጣቱን ትውልድ በዘረና በቋንቋ ከፋፍሎ ትግሉን ለማኮላሸት የተሞከረውን የወያኔን ተንኮል አክሽፎ ፤ ዳግማዊ የካቲትን መስል ምዕራፍ ከፈተ። ፋኖው፤ የኦሮም ደም የኔ ደም ነው ብሎ መልዕክት ሲያስተላልፍለት፤ ቆሮው በመልሱ፤ ኢትዮጵያን ኬኛ ! ብሎ አስተጋባ። ይኸ ማስተጋባት ፤ የወያኔን ጎራ ፈረካከሰው። የከፋፍለህ ግዛው መሰሪ ተንኮል ተፍረከረከ። የዘረኛ አገዛዝ አራማጆች፤ በየስርቻቸው ተሸሽገዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት አዲስ ምዕራፍ ከፈተ። ሕዝባችንም የፖለቲካ ብስለቱንና ጥበቡን በተግባር አስመሰከረ፡፡ ሠላማዊ ለውጡን በሠለጠነ መንገድ አስተናገደ። ዘውጋዊ ፖለቲካን ወደ ሀገራዊ ራዕይ ለወጠው። ለሀገራችን ወጣት ትውልድ ምሥጋና ይግባው ! የነገዋን ሃገሩን ተረካቢው እርሱ እራሱ መሆኑ፤ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። ለመጭው ብሩኅ ተስፋ፤ ብርቱ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ጥንቅቆ ያውቃል ።ሀገሪቱ ሰፊና ሀብታም፤ ህዝቧ ታላቅ፤ ጉራማሌና ታታሪ ፤ ምድሯ በለፀጋ፤ ታሪኳ ረዥምና ገናና እንደሆነ ጠንቅቆ ተረድቷል። ማንም ከፋፋይ ሊያታልለው አልቻለም። በከፋፋዮች የወደቀጭችውን ሀገር እያነሳ፤ ቀደምት ዐርብኞችንና ሠማዕታትን ሳይረሳ፤ ሀገሩን እየገነባ መፃዒ ዕድሉን እያስተካከል ሀገሩን ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ያሸጋግራታል። ኢትዮጵያም ለዘለዓለም በአንድነቷ መኖሯን ትቀጥልበታልች ። ታውቅበታለችም!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !